$1 CAN

# ሐ·ዋ·ር·ያ

# HAWARYA

ቅጽ 15 | ቁ. 9 | ፋክስ (905)799-2193 | መጋቢት 2002

Vol 15 | Issue 9 | Tel (416) 459-5964 | March 2010 | www.hawarya.net | hawarya.publications@sympatico.ca




## VANOC THANKS CANADIANS

### OVER 3.5 MILLION PAIRS OF RED MITTENS PURCHASED IN SUPPORT OF CANADIAN WINTER ATHLETES



Vancouver, BC - The Vancouver Organizing Committee for the 2010 Olympic and Paralympic Winter Games (VANOC) today thanked Canadians and all fans who showed their support for the Canadian athletes and the 2010 Games by purchasing a pair of Red Mittens. Over 3.5 million pairs of mittens were sold during the five-month campaign and the mittens quickly became one of the most enduring and popular items of the pre-Games and Games-time period. The full inventory of Red Mittens has now been sold.

"To everyone who bought a pair of Red Mittens, who waved at a torchbearer in their community, who showed their spirit every day, or who wore them while cheering their team at the venues or while watching on television, we send a heartfelt

*continued on p(21)*

## ለማህበረሰብ የብዙሃን መገናኛዎች መግለጫ ተሰጠ




Elizabeth May (left), Adriane Carr (center) and Ellen Michelson

በቶሮንቶና አካባቢው ለሚገኙ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ የብዙሃን መገናኛ አውታሮች የካናዳ ግሪን ፓርቲ Green Party of Canada) ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ። መግለጫውን የሰጡት የሰጡት የፓርቲው መሪ እመት ኤልሳቤጥ ሜይ (Elizabeth May) ሲሆኑ የፓርቲው ምክትል መሪና የቅርስና ባህል ተጠሪ አድሪያን ካር (Adriane Carr) አብረዋቸው ተገኝተዋል። ከሁለቱ መሪዎች በተጨማሪም ለቶሮንቶ-ዳንፎርዝ፣ ለመካከለኛው ቶሮንቶና ለኦክ ሪጅስ -ማርከሃም (Toronto-Danforth, Toronto Center & Oak Ridges-Markham) በስማቸው ቅደም ተከተል ለመጭው ሀገር አቀፍ ምርጫ ለፌደራሉ ፓርላሜንት የካናዳን ግሪን ፓርቲ በመወከል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው የተመደቡት እመት አድሪያና ሙኛቶ-ሃሙ፣ እመት ኤለን ሚቸልሰንና ሚስተር ትሪፎን ሃይታስ (Adriana Mugnatto-Hamu, Ellen Michelson & Trifon Haitas) ተገኝተዋል።

**ወደ ገጽ** 22 **ዞሯል**




"ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሄር" መዝ 115፣6
"የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሄር ፊት የከበረ ነው" መዝ 115፣6

## የብፁዕ አባታችን አቡነ ዜና ማርቆስን እረፍት በተመለከተ ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ

በቅድስት አገር በኢትዮጵያም ሆነ በስደት ዓለም ያለውን ሕዝብ ከልጅነት እስከ እውቀት በፍቅርና በታማኝነት ሲያገለግሉ የነበሩት ታላቁ አርቶዶክሳዊ አባት ሊቀ ጳጳስ ብፁእ አቡነ ዜና ማርቆስ ቅዳሜ የካቲት 6 ቀን 2 ሺህ 2 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን በሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል የሚገኘው የብፁእነታቸው መንበረ ጵጵስና ጽ/ቤት ገልጿል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታላቁን መንፈሳዊ አባት ብፁእ አቡነ ዜና ማርቆስን በማጣቷ ታላቅ ሐዘን ላይ ትገኛለች። በተለይም ቤተ ክርስቲያን በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት ታላቁ አባታችን ከእኛ በሥጋ መለየታቸው ቅዱስ ሲኖዶሱን አሳዝኖታል።



ልደት፣ እድገትና ትምህርት:-

ታላቁ አባት ብፁእ አቡነ ዜና ማርቆስ በቅድስት አገር በlትዮጵያ በጎንደር ክፍለ ሃገር በእብናት ወረዳ ደጋ መልዛ ከስመ ጥሩዋ ሹምጌ ማርያም አጠገብ ከሚገኝ ቅብቲያ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እግዚAብሔርን ከሚፈሩ ወላጆቻቸው አቶ በጎ ሰው ወልደ ጻድቅ እና ወይዘሮ ገነት ወልደ ጊዮርጊስ ጥቅምት 22 ቀን 1930 ዓ.ም ተወለዱ። ከልጅነት እድሜያቸው ጀምሮ እግዚ

**ወደ ገጽ** 20 **ዞሯል**

## የአድዋ ድል ታሰበ



በየዓመቱ የሚከበረው ታሪካዊው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል በዚህ ዓመትም ታስቦ ውሉዋል። የዘንድሮው 114ኛ የአድዋ ድል መታሰቢያ በሀገር ቤትና በተለያዩ የውጭ ሀገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በልዩ ድምቀት ያከበሩት ሲሆን በቶሮንቶ (ካናዳ) የተካሄደው አንዱ ነበር።

በቶሮንቶ ውስጥ ከዚህ ቀደም ሲደረግ እንደቆየው ሁሉ 114ኛውን የአድዋ ድል መታሰቢያ ያዘጋጀው የኢትዮጵያዊያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ሲሆን፣ በአሉን የደመቀና የተሳካ ለማድረግ ማህበሩ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን ማወቅ ተችሉዋል። 40 ዶንላንድ ላይ በሚገኘው የግሪኮች የስብሰባ አደራሽ ውስጥ በተካሄደው የቶርንቶ 114ኛ ዓመት

**ወደ ገጽ** 23 **ዞሯል**







